**ROYAL CHILDREN'S HOSPITAL**

ለርስዎና ለልጆች ንጹሕ አየር

የሮያል ህፃናት ሆስፒታል ከሲጋራ ሽታ ነፃ የሆነ አካባቢ ለህፃናት ያቀርባል።
ከሲጋራ ጪስ ነፃ የሆነ አካባቢ በመፍጠር ህፃናት የተሻለ ጤና እንዲኖራቸው ይረዳል።

ልጅዎት ወደ ሮያል የህፃናት ሆስፒታል በሚጎበኙበት ጊዜ እርስዎም ሆኑ ቤተሰብዎ በቤትዎና በመኪናዎ አካባቢ ጪስ እንዳይኖር ለመማር እድል ይሰጣል።

አሁን በሮያል የህፃናት ሆስፒታል የሚገኙ ህንጻዎችና ሜዳዎች ከጪስ ነፃ አካባቢ ናቸው። ስለ ማጨስ በሆስፒታሉ ያለውን ፖሊሲና ለማጨስ ለሚፈልጉ የት ሄደው ማጨስ እወንዳለባቸው በዚህ በራሪ ወረቀት ማብራሪያ የቀረበ ሲሆን ስለ ሲጋራ ማቆም ምን ዓይነት አገልግሎት እንደሚሰጥ በዚህ በራሪ ወረቀት ይቀርባል።

ሰዎች ህፃን ወደ ሆስፒታል በሚወስዱበት ጊዜ በጣም ያስጨንቃል እና በጭንቅ ጊዜ ብዙ ሰዎች ሲጋራ ያጨሳሉ። ብዛት ያላቸው አዋቂዎች ለኒኮቲን የሱሰ ተገዢ ሲሆኑ በዚህ አካባቢ ለመቆየት እንደማይፈልጉ ይረዳናል!

በዚህ ምክንያት የተነሳ በሆስፒታሉ አካባቢ እንዳያጨሱ ከማስገደድ ሶስት የታወቁ ቦታዎችን ሆስፒታሉ በመለየት ማጨስ ሲፈቀድ በህንጻው ውስጥ ማጨስ ግን አይፈቀድም።

ልጅዎ በሆስፒታሉ ውስጥ ሲኖር ማጨስ ከፈለጉ ለማጨስ በተመደቡት ቦታ ላይ ሄደው እንዲያጨሱ እናሳስባለን። እነዚህ ቦታዎች ወደ ሆስፒታሉ ንጹሕ አየር ከሚገባበት ቦታ የራቁ ናቸው። በንጹሕ አየር ማስገቢያው አካባቢ ሆኖ ማጨስ ከአየሩ ጋር ወደ ሆስፒታሉ ውስጥ በመግባት ጥብቅ ከትትልና እንክብካቤ ለሚደረግላቸውና በአልጋ ላይ ያሉትን ህፃናት ጤና ስለሚችል ነው።

በዚህ በራሪ ወረቀት ላይ ለማጨስ የታቀዱትን አካባቢዎች ማፕ/ስእል ያሳያል። ከዚህ አካባቢ ውጪ ማንም ሰው ሲያጨስ ሲጋራውን እንዲያጠፋ ወይም ከአካባቢው እንዲርቅ ይጠየቃል።
በትንባሆ የተበከለ አካባቢና ሌላ ሰው ሲጋራ ሲያጨስ በህፃናት ጤና ላይ ችግር እንዳለው የታወቀ ነው።

ወላጆች ሲጋራ የሚያጨሱ ከሆነ በህፃናት ደም፤ ሽንትና ምራቅ ምርመራ ላይ እንደሚገኝ ነው።
ህፃናት ሌላው ሰው ሲያጨስ አብረው ከተጋለጡ ከዚህ በታች ላለው ያስከትላል:

በደረት ላይ ችግር እንደ:
- አስም
- ብሮንክሊቲስ
- የሳንባ ምች
- የትንፋሽ እጥረት
- የጆሮ ቁስለት
- የጉሮሮ ብግነት
- የህፃናት በቅጽፈት የመሞት ችግር
- ኃይለኛ የሆነ የባክቴሪያ ብግነት/ቁስለት

ሲጃራ ከሚያጨሱ ወላጆች ጋር የሚኖሩ ህፃናት እነዚህ ሁኔታዎች ስለሚያጋጥማቸው ሆስፒታል የመግባት እድላቸው ከፍተኛ ይሆናል።

አብዛኛው የሚያጨሱ ወላጆች ባልጀምር ደስ ይለኝ ነበር ይላሉ። ህፃናት ከሚያጨሱ ወላጆች ወይም ወላጅ ጋር ካደጉ በአብዛኛው አጫሽ እንደሚሆኑ ነው። ወላጆች ማጨስ በማቆማቸው ተከከለኛ እርምጃ እንደሆነና ለራሳቸው ጤንነትና ለወደፊት የልጆቻቸውን ጤንነት መጠበቅ እንደሚቻል ነው። ምንም እንኳን ለልጆቻቸው አታጭሱ ቢሏቸውም ወላጆች ታላቁ የኩረጃ አርኣያ እንደሚሆኑ ነው። እነሱም ወላጆች ያደረጉትን ለመቅዳት እንጂ የሚሉትን አይሰሙም።

ሲጃራ ለማቆም የፈለጉ ሰዎች ምን ዓይነት አገልግሎት ይኖራል?
ከአራት አዋቂ አጫሾች ውስጥ ሶስቱ የሚችሉ ከሆነ ማጨስ ለማቆም እንደሚፈልጉ ነው። ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ደግሞ ለማቆም እንደሚያስቡ ነው። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ወደ ሮያል የህፃናት ሆስፒታል መጎብኘት ይበጅ ይሆናል! ከልጅዎት ሐኪም ወይም ነርስ ጋር ስለ ማጨስ ማቆም የሚቻልበትን ማነጋገሩ ይበጃል እንላለን።

እንዲሁም የሚከተለውን ቢያናግሩ እንላለን
ማጨስ ለማቆም መስመር/Quitline በስልክ: 131 848
ይህ በቪክተሪያ ማቆም/QUIT በኩል በስልክ የሚሰጥ ማብራሪያና የምክር አገልግሎት ይሆናል። መረጃና የተለያየ የነፃ አገልግሎት እንዴት ማግኘት እንደሚችሉ በሰለጠኑ ሠራተኞች ይስተናገዳሉ። ለስልክ ጥሪ ክፍያ በአካባቢ ሂሳብ ይሆናል

Amharic

የርስዎ ቤተሰብ ሐኪም አጠቃላይ ባለሙያ/GPs ሰዎች እንዴት ሲጃራ ማቆም እንደሚቻል ይረዳሉ። ስለ የተለያዩ አማራጭ ሁኔታዎች ማናገር ይህም ሕክምና ማለት ዚይባን/Zyban እና ኒኮቲን/nicotine ለመተካት የሚችሉ [እንደ የሚለጠፍና የሚታኙ] እንዲሁም ሌሎች እርዳታዎችን ያካተተ ይሆናል።

የቀረበው በ:

ሲሆን ተባባሪዎች:

Amharic


AMBULANCE BAY
EMERGENCY ENTRANCE
SMOKING
SOUTH EAST BUILDING
GATEHOUSE STREET


RECEPTION
RAMP UP
UP
DOWN
TELEPHONE
LIFTS
MCDONALDS
ATM
MAIN ENTRANCE
SMOKING


HELIPAD
(ROYAL PARK)
SQUASH COURT
PLAYGROUND
SMOKING
CAFÉ GARDEN
TO
GATEHOUSE
STREET
CAR PARK
CAFÉ – REAR FIRST FLOOR MAIN BUILDING